# ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ

# Coalition for Unity and Democracy Party (Kinijit)

***http://www.kinijitethiopia.org***

e-mail kil@kinijitinternational.org Voice Mail/Fax 1-206-203-3974


**ጋዜጣዊ መግለጫ**

**ኪል -007/07**
**የካቲት 12 ቀን 1999 ዓ.ም**

## *ነጻነት ከሌለው ፍርድ ቤትና ህሊና ከሌላቸው ዳኞች ፍትህ እንደማይገኝ የታወቀ ነው*

ከህግና ከፍትህ ውጭ ያለአግባብ የሃሰት ክስ ተመስርቶባቸው አበሳቸውን የሚያዩትን የቅንጅት መሪዎች፣ ጋዜጠኞችና የሰብአዊ መብት ተሟጋቾች እጣ የሚወስን ብይን ይሰጣል የተባለው ፍርድ ቤት እንደተጠበቀው ምንም ሳይወስን ቀነ ቀጠሮ ሰጥቶ ዛሬ የካቲት 12 1999 ተበትኗል:: የህሊና እስረኞቹ ጉዳይ እልባት ሳያገኝ ለአስራ አምስት ቀን የመቅጠሩ ውሳኔ በመለስ ዜናዊ በሚመራው የፖለቲከኞች ቡድን አስቀድሞ የተወሰነና ለዳኞቹም ትእዛዙ እንደተላለፈ ቅንጀት ለአንድነት ለዴሞክራሲ ለኢትዮጵያ ህዝብ ከሳምንት በፊት መግለጫ ያወጣበት ጉዳይ እንደሆነ ይታወሳል:: በመሆኑም ዛሬ የካቲት 12 1999 ያስቻለው ችሎት

1ኛ አቶ ሃይሉ ሻውል በአሜሪካ ፕሬስ ክለብ ያደረጉት የእንግሊዝኛ ንግግር ወደ አማርኛ ተተርጉሞ፤

2ኛ በእንግሊዝኛ የተጻፉ ከድረ-ገጽ የተወሰዱ ሰነዶች በአማርኛ ተተርጉመው

3ኛ የምርጫ ቦርድ የመጨረሻውን የምርጫ ውጤት ሰነድ ይቅረብልን የሚሉ ሶስት ሰንካላ ምክንያቶችን በመዘርዘር ሌላ ቀጠሮ ለየካቲት 26 1999 ሰጥቶ መበተኑ ዳኞች በትእዛዝ እንደሚሰሩ፣ ነጻ ፍርድ ቤትና የፍትህ ስርአት እንደሌለ ለምናውቀው የሃገሪቱ ዜጎችና የአለምአቀፉ ህብረተሰብ የሚያስገርም አይደለም::

የዛሬው የፍርድ ቤት ውሎ የሚያረጋግጠው በኢትዮጵያ ውስጥ የፍትህ ስርአቱን እንዳሻው የሚቀልድበት አምባገነናዊ ስርአት መንገሱን ነው:: ይህንን ስርአት የህግ የበላይነት በነገሰበት ስርአት ለመተካት የኢትዮጵያ ህዝብ መራራ ትግል ይጠብቀዋል:: የቅንጅት መሪዎች ጋዜጠኞች የሰብአዊ መብት ተሟጋቾችና የሀገሪቱን የማኅሪያ ጣቢያዎች ያስጨነቁትን በሽዎች የሚቆጠሩ የፖለቲካ እስረኞችን ማስፈታት የሚቻለው፣ እብሪት የሚሰሩትን ያሳጣቸውን ገዥዎችና እነዚህ ገዥዎች እንደ ቤት ሰራተኞቻቸው ከሚያዟቸው ዳኞች እንዳልሆነ መረዳት ይኖርብናል::

የወያኔ/ኢህአዴግ ፍርድ ቤቶች መታሰር የማይገባቸውን ንጹሃን ዜጎች እያሰሩ በፍትህ ስም በቀነ ቀጠሮ በማንገላታት በእስር ቤት ረጅም ግዜ ያለምንም ብያኔ በማኖር ወይም በእስር ቤት ውስጥ በበሽታ እንዲያልቁ ማድርግ የሰለጠኑበት ጥበብ ሆኗል:: ይህ የዛሬው ውሳኔ ወያኔ በቅንጅት መሪዎችና በሌሎችም እስረኞች ላይ በፍትህ ስም ሊያኪያሂድ ያሰበውን የበቀል እርምጃ የሚጠቁም ነው:: የኢትዮጵያ ህዝብ በድምጹ የመረጣቸውን መሪዎቹን፣ አንደበት ሆነው ያገለገሉትን ጋዜጠኞቹንና የመብቱ ተሟጋቾችን በፍርድ ቤት ቀጠሮ እያንገላቱ፣ አእምሯቸውንና አካላቸውን ለስቃይ እየዳረጉ ተራ በተራ ለመፍጀት ወያኔ/ኢህአዴግ የሸረበውን ሴራ መበጣጠስ የራሱ የኢትዮጵያ ህዝብ ሃላፊነት ነው:: በሃገር ውስጥና በሃገር ውጭ የተጀመረውን ትግል በማቀጣጠል ለኢትየጵያና ለህዝቧ ሲሉ መከራቸውን የሚያዩትን የህሊና እስረኞች በሙሉ አንድም ሳይቀር ማስፈታትና እንዲህ አይነቱ ፍህትህ ረጋጭ ስርአት በሃገራችን ዳግም እንዳይነግስ ማድረግ በሁሉም ኢትዮጵያዊ ላይ የተጣለ ታሪካዊና የዜግነት ግዴታ ነው::

**ለፍትህ ለነጻነት ለዴሞክራሲ ለሰላምና ለእርቅ በሃገር ውስጥና ከሃገር ውጭ የተጀመረው ትግል ይቀጥላል!**

**በኢትዮጵያችን ነጻ ፍርድ ቤቶችንና ለህሊናቸው የሚፈርዱ ዳኞች የምናይበት ቀን እሩቅ አይደለም!**

**ቅንጅት ለአንድነትና ዴሞክራሲ ፓርቲ**